# ፍትሕ የጠማው ህዝብ

## እውነት ህወሓት የትግራይ ህዝብ ነፃ አውጪ?

ክፍል 2

ይኩኖ መስፍን
ቦስተን ማሳቹሰት

ባለፈው ክፍል አንድ ፅሑፌ “ቀበሮ የበግ ለምድ ለብሶ ፍየሌን ቀማኝ” እንዳሉ ሁሉ ህወሓት/ኢህአዴግ የነፃነት ካባ ለብሶ በዲሞክራሲ ስም ታግሎ መንበረ ስልጣኑን ካመቻቸ በኋላ መልሶ የኢትዮጵያን ህዝብ ነፃንት የነጠቀና የመቶ ሽዎችን ሰማእታት አደራ የሰበረ የክህደት ስብስብ መሆኑን ከተግባሩ በላይ ሌላ ምስክር የሚያስፈልግ አይመስለኝም። ሁላችንም ካለፈው ልምዳችን እንደምናውቀው የኢትዮጵያ ህዝብ ታሪክ የነፃነት ትግል ታሪክ ቢሆንም ታግሎ ያገኘውን የድል ችቦ በተደጋጋሚ በጥቂት አንባገነኖች በአቋራጭ እየተነጠቀ፣ የተከፈለውን የነፃነት ዋጋ (መስዋእትነት) ውጤቱ ታጥቦ ጭቃ እየሆነ በመምጣቱ እነሆ ዛሬም ኢትዮጵያ እናታችን በዓለም ማሕበረሰብ ዘንድ የረሃብ፣ የጦርነት፣ የዝርፊያ፣ የአፈና፣ የጭቆናና የልመና ተምሳሌት ሆና እንድትታይ አድርጓታል” በሚሉ ርእሰ ጉዳዮችና በተለይም በአሁኑ ጊዜ ህዝባችን በምን ሁኔታ ላይ ይገኛል? በስልጣን ላይ ያለው ቡድን የሚለውንና በመሬት ላይ ያለውን እውነታ ምን ይመስላል? በሚሉት ወቅታዊ ጉዳዮችና ሌሎች ነጥቦች ዙሪያ ጭብጥ መረጃዎችን መሰረት በማድረግ አንኳር አንኳር በሆኑት ችግሮች ላይ ብቻ በማትኮር ለመዳሰስ ሞክሬ እንደነበር ይታወሳል። እነዚህ ፅሑፎች በተከታታይ ለማቅረብ ካነሳሱኝ ነገሮች አንዱ በቅርብ ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ በአካል ተዘዋዉሬ በዓይኔ ያየኋቸውና እንዲሁም በቀጥታ የችግሩ ሰለባ ከሆነው ከራሱ ከህዝቡ አንደበት ያገኘኋቸው ጭብጥ መረጃዎች ሕብረተሰቡ ማወቅ አለበት የሚል እምነት ስላደረብኝ ነው። በመሆኑም የዛሬው ክፍል ሁለት ፅሑፌም ካለፈው የቀጠለ ሲሆን በአቀራረቡም በሚከተሉት ወቅታዊና አንገብጋቢ ጉዳዮች ላይ በማትኮር በቀደም ተከተል ቀርቧል።

## እውነት ህወሓት የትግራይ ህዝብ ነፃ አውጪ?

በክፍል አንድ እንደተጠቀሰው የትግራይ ህዝብ በህወሓት ሞኖፓላዊ አገዛዝ ስር ከገባ እንሆ 38 ዓመታት አስቆጥሯል። በነዚህ አራቱ አሰርቱ ዓመታት ውስጥ በተለያየ መልኩ በህወሓት ቤቱ ያልተንኳኳ ወይም ያልተነካ የትግራይ ገበሬና ከተሜ የለም ቢባል ማጋነን አይሆንብኝም። ቁጥራቸው 60 ሽሕ በላይ የሚገመቱ ወጣቶች ከደርግ ጋር በተደረገው ፍልሚያ ህይወታቸውን አጥቷል። በአስር ሽዎች የሚገመቱ ለጋ ወጣቶች ኤርትራን ነፃ ለማውጣት በኤራትራ በራሃዎች ደማቸውን ፈሷል። ከኢ..ድ.ዩ እና ከኢሕአፓ ጋር በተደረገው የርስ በርስ ፊልሚያ በሽዎች የሚገመቱ ወጣቶች ሞቷል። ከጅብሃ ጋር በተደረገው ውጊያም በርካታ ወጣቶች ሂይወታቸውን አልፏል። የዚህ ሁሉ እልቂት በህዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ (ህወሓት) አገላለፅ ለነፃነት፣ ለፍትሕና ለዲሞክራሲ ተብሎ የተከፈለ ክቡር መስዋእትነት ነው እየተባለ ነበር የሚነገረን።

መስዋእትነቱ በዚህ ብቻ አላቋረጠም። ከደርግ ውድቀት በኋላም በሀገር መከላሊያ ስም ከኦሮሞ ነፃ አውጪ (ኦነግ) እና ከኦጋዴን ነፃ አውጪ ድርጅቶች ጋር በተደጋጋሚ ሲካሄድ በቆየው ጦርነት ምክንያት የተከፈለው የሂይወት ዋጋም ቀላል አይደለም። ከሁሉም በላይ ደግሞ ከድንበር ውዝግብ ጋር በተያያዘ ጉዳይ ዳግም ከኤርትራ ከሻዕቢያ ጋር የተካሄደው ጦርነትም በአስር ሽዎች የሚገመት ሰራዊት አልቋል። በነዚህ ተደጋገሚ ጦርነቶች ምክንያት ተንከባካቢ ያጡ አካል ጉዳተኞች፣ ጧሪ አልባ ሆነው የቀሩት አረጋውያንና ወላጅ አልባና የጎዳና ተዳዳሪ ሆነው ለልመናና ለአስፀያፊ ስራ የተዳረጉት ለጋ ህፃናትም ቁጥራቸወ ቀላል አይደለም። ይህ ሁሉ ድምር መስዋእትነትም አሁንም እንደተለመደው በህወሓ መሪዎች

አገላለፅ “የትግራይ ህዝብ ነፃ ለማውጣት ብሎም ሀገራችንንና ዲሞክራሲያዊ ስርዓታችንን ለመጠበቅ ተብሎ የተከፈለ ዋጋ ነው” ይሉናል።

ይሁን እንጂ ጥያቄው ለምን ይህ ሁሉ መስዋእትነት ተከፈለ? ለተከፈለው መስዋእትነትስ መንሲኤውና ተጠያቂው ማን ነው? የሚለው ብቻ አይደለም መታየት ያለበት። ዋናው መመለስ ያለበት አወዛጋቢ ጥያቄ የኢትዮጵያ ህዝብ በተለይም የትግራይ ህዝብ ይህ ሁሉ መስዋእትነት ተከፍሎ ምን ለውጥ አገኘ? በሰማእታት ስም የለውጡ ተጠቃሚ እየሆነ ያለውስ ማን ነው? የሚለው ነው። በትግሉ ሂደት ወንድሞቼ፣ የቅርብና የሩቅ የስጋ ዘመዶቼ፣ ጎረቤቶቼና ሌሎች ለጋ ወጣት ጓደኞቼ የተሰዉ እንዳሉ አውቃለሁ። ለነዚህ ሰማዕታት ያለኝን ክብር ምንም ጊዜም የሚለወጥ አይደለም። ነገር ግን በተለያዩ ጊዚያት ወደ ሀገር ቤት በሄድኩ ቁጥር ለተከፈለው መስዋእትነት የማይመጥኑና የሰማእታቱን አላማ የሚፃረሩ የመልካም አስተዳደር ጉደለቶች በግልፅ ይታዩኝ ነበር። እኔም አንዳንዶቹ ተራ የአሰራር ጉድለቶች እየመሰለኝ ከህዝቡም ከአንዳንድ ባለስልጣናትም ጭምር በአካል ስለጉዳዩ እየተነጋገርኩኝ አልፎ አልፎም በፅሑፍ መልክ ያለኝን ቅሬታ አቀርብ ነበር። በአጋጣሚ በቅርብ ጊዜ ወደ ሀገር ቤት ሄጄ ያየሁት አስገራሚና አሳዛኝ የሆነ ሁኔታ ግን ከምናገረው በላይ ሆኖ አግኝቸዋለሁ። በዚህ ምክንያትም “እውነት ህወሓት የትግራይ ህዝብ ነፃ አውጪ? የሚለውን ጥያቄ ደጋግሜ እንዳነሳ አድርጎኛል።ችግሩ በዚሁ ሁኔታ ከቀጠለ ሀገሪትዋስ ወዴት እያመራች ነው? የሚለው ጥያቄም ሀገር ወዳድና የህዝብ ወገን የሆነ ሁሉ ሊያሳስበውና ሊያስጨንቀው የሚገባ ጉዳይ ነው።

- ህዝብና መንግስት ሆድና ጀርባ ናቸው ብቻ ሳይሆን አንዳንድ ጊዜም በግልፅ የሚሰራው ድራማ ስታይ መንግስት አለ ወይ? ብሎ ለማመንም ያዳግታል። ህዝቡ አቤት የሚልበትና ችግሩ የሚገልፅበት ነፃ የፍትሕ ቦታና ሁኔታ አይታይም። የመንግስት አካላት አሉ ቢባልም የቆሙት ለህዝቡ ልዕልና ሳይሆን ለአንድ ድርጅት ጥብቅና ነው። የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ታማኝ ላልሆነ ዜጋ የፍትሕ በሩ ዝግ ነው። የመንግስት አካላት የህዝቡን ድህንነት የሚጠብቁና ሕግን የሚያስከብሩ ሳይሆን ለራሳቸው ከሕግ በላይ ሆነው ህዝቡን የሚያሸብሩ ናቸው። በአካባቢው የተሰማሩ ካድሬዎችና ባለስልጣናት የሕብረተሰቡን ችግር የሚፈቱ ሳይሆን ችግሩን የበለጠ እንዲባባስ በማድረግ በአንድ በኩል ህዝቡ በፍርሃት ፀጥ ረጭ ብሎ አሜን ብሎ እንዲገዛላቸው በሌላ በኩል ደግሞ በግርግሩ የግል ጥቅማቸውንና ስልጣናቸውን ለማጠናከር እንደ መሳሪያነት ይጠቀሙበታል። ለምሳሌ ረሃብን እንደ መለመኛ መሳሪያ ብቻ ሳይሆን ታማኝ አባላትን የሚመለሙሉበት ትልቁ ማምረቻ ነው። በአንፃሩ ተቃዋሚ ወይም አፈንጋጭ ብለው ለሚጠረጡሩት ሰው ደግሞ በሆዱ ለመቅጣት የሚገለገሉበት የፓለቲካ መሳሪያቸው ነው።

- የትግራይ ህዝብ አማራጭ ሃሳብና አማራጭ መድረክ የሌለው በአንድ ድርጅት በህወሓት በጅሆ (ሆስቴጅ) የታያዘ ህዝብ ነው። በክልሉ የሚገኘው አስተዳደር የመንግስት መዋቅር ደንብ የተከተለ ነው ይባል እንጂ ህዝቡ ሕገ መንግስቱን አይመለከተውም። የሚተዳደረው ልክ በትጥቅ ትግሉ ዘመን እንደነበረው ዓይነት በሲቪል ለበስ ታማኝ ካድሬዎች ነው። በአንዳንድ አፈና የነገሰባቸው ሀገሮች የፓሊስ ስቴት ተብለው እንደሚጠሩት ሁሉ ትግራይም የካድሬ ክልል እየተባለች ትጠራለች።

- ትግራይ ከማንም ጊዜ በላይ አፈና፣ ስጋት፣ ፍርሃትና ሽብር የነገሰባት ክልል ሆናለች። ለአቶ መለስ ዜናዊ ስልጣን አስጊ ናቸው የሚባሉ እንደነ መድረክ፣ አንድነት፣ አረናና ሌሎች ተቃዋሚ የፓለቲካ ድርጅቶች አባላት ወይም ደጋፊ ተብለው የሚጠረጠሩ ሁሉ ሰበብ አስባብ እየተፈለገባቸው እስር ቤት ማጎር፣ ከስራ ማባረር፣ ከየድርጅታቸው አባልነት እንዲወጡ በጥቅም መደለል ካልሆነ ደግሞ በማስፈራራት እንዲገለሉ ማድረግ፣ ከያሉበት እየታፈኑ እንዲሰውሩ ማድረግ፣ በተለያየ ጫና ሀገር ለቀው እንዲሰደዱ መገፋፋት የመሳሰሉ የአፈና ድርጊቶች የተለመዱ የካድሬው መደበኛ ስራዎች ናቸው። ለምሳሌ በነ አንዳለምና እስክንድር ነጋ የተፈፀመው ኢ-ፍትሓዊ ድርጊት አልበቃ ብሏቸው

ሰሞኑን በተመሳሳይ ሁኔታ በትግራይ በዓረና አባላት ላይ የሚያካሂዱት የመንጥር ዘመቻቸው በተጠናከረ መልኩ ቀጥሏል። ለምሳሌ አቶ ጎይተኦም ፀጋይ በቴምቤን መምህር፣ አቶ አያሌው በየነ በሽሬ እንዳስላሴ፣ አቶ ተወልደ አማረ በመቀሌ ከነበሩበት ስራ እንዲባረሩ ተደርጓል። በተጨማሪም የአረና ምክትል ሊቀ መንበር የሆኑት አቶ ብርሃኑ በርሄ ለሁለት ወር ያህል በሰሜን አሜሪካ በስራ ጉዳይ ሲንቀሳቀሱ ቆይተው ወደ ሀገር ቤት ከተመለሱ በኋላ አንድ ሳምንት ባልሞላ ውስጥ በረቀቀና በተደራጀ መልክ ማንነታቸው ባልታወቁ ሰዎች ቢሮዋቸው ከነ ሙሉ ንብረቱንና ደመኩሜንቶቹን በሌሊት ተዘርፏል። በአጠቃላይ ለያንዳንዱ የዓረና አባል ወይም የተቃዋሚ ድርጅቶች አባል ወይም ደጋፊ ነው ብለው ለሚጠረጥሩት ሁሉ እንቅስቃሴውን በዓይነ ቁራኛ የሚከታተሉ ከሁለት በላይ የድህንነት አባላት ተመድበውበታል።

- የትግራይ ህዝብ ዛሬም ከጥይት ጭኸትና ከጦርነት ስጋት አልተላቀቀም። ከላይ እንደተጠቀሰው የትግራይ ህዝብ ከትጥቅ ትግሉ ጀምሮ በሻዕቢያና በህወሓት መሪዎች በሁለት አለንጋ እየተገረፈ እንደመጣ ሁሉ ዛሬም በባሰ መልኩ ቀጥለዋል። በቅርቡ “ዴሞክራሲያዊ ምንቅስቓስ ህዝቢ ትግራይ” (ደምህት) ብሎ ራሱን የሚጠራ በሻዕቢያ የሚንቀሳቀስ የፓለቲካ ድርጅት በትግራይ መሬት እየገባ በአንዳንድ ወታደራዊ ምሽጎችም ሆነ በሰላማዊ ህዝቡ ላይ ጦርነት በመክፈትና ፈንጅ በመቅበር ተደጋጋሚ ጥቃቶች እንደሚፈፅም ይታወቃል። ይሁን እንጂ በህዝቡ እየደረሰ ያለው ጥቃት አንድ ቀን እንኳን በብዙሃን መገናኛ ተገልፆ አያውቅም። በአንዳንድ ከተሞችም በስውር ሰርጎ እየገባ የስልክ መገናኛዎች እንዲቋረጡ በማድረግ የህዝቡን ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሂይወት እንዲናጋ ያደርጋል። አንዳንድ ጊዜም በህወሓት አባላት ውስጥም ሰርጎ በመግባት በገንዘብም ሆነ በሌላ ነገሮች በመደለል የሻዕቢያ ተልእኮ ማስፈፀሚያ እንዲሆኑ እያደረገ ይገኛል። ለምሳሌ በምዕራብ ትግራይ ቢራራ በሚባል ልዩ ስፍራ የወጣቶች አስተባባሪ ሆኖ ይሰራ የነበረ አንድ የህወሓት አባል $2000 ብር ተከፍሎት በአንድ የህዝብ ማመላለሻ አውቶቡስ ውስጥ ፈንጅ በመቅበር የ16 ንፁኃን ዜጎች ሂይወት መጥፋት ምክንያት ሆኗል። ካድሬው ወንጀሉ ከፈፀመ በኋላ በቁጥጥር ስር ውሎ እስር ቤት እንደሚገኝ ያካባቢው ሰዎች ገልፀዋል። ይህንንም በብዙሃን መገናኛ ገና በይፋ አልተገለፀም።

  ከዚሁ ተደጋጋሚ ችግር በመነሳት ህዝቡ ዓቅምና አማራጭ መንገድ አጣ እንጂ ሻዕቢያና የአቶ መለስ ዜናዊ አገዛዞች ስልጣን ላይ እስካሉ ድረስ የኤርትራ አጀንዳ መቋጫ የሌለው የኢትዮጵያ ህዝብ በተለይም የትግራይ ህዝብ ዕዳና ፍዳ ሆኖ እንደሚቀጥል አያጠራጥርም የሚል ድምዳሜ ከደረሰ ውሎ አድሯል። ይህን ጠንቅቆ የተረዳ የአቶ መለስ ዜናዊ ቡድንም በኢትዮጵያ ተቀናቃኝ ሀይል ብቻ ሳይሆን ስለሀገሩ፣ ስለሰብአዊ ክብሩንና ሉዓላዊነት ማንነቱን በአደባባይ ጥብቅና ለመቆም የሚችል፣ በራሱና በህዝቡ የሚተማመን ብሄረተኛ ዜጋ እንዳይበቅል ሆን ብሎ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ እያጠፋው ይገኛል። በምትኩ ስብእናውንና ነፃነቱን አሳልፎ የሰጠ፣ ጥያቄ የማያስነሳ፣ በአብዮታዊ ዲሞክራሲ የማሌሊት ፍልስፍና ተጠምቆ ወኔው የተኰላሸ ዜጋ ሆኖ እንዲያድግ ለማድረግ በከፍተኛ ደረጃ እየተንቀሳቀሰበት ይገኛል። በሌላ በኩል ደግሞ እንደ መድረክ የመሳሰሉት ተቀናቃኝ ድርጅቶች ለማክሰም ቀጣይነት ያለው የመኰርኰም እርምጃ እየወሰደ ይገኛል። በነዚህ ድርጅቶች አባላት ላይ በየቀኑ እየተፈፀመ ያለው የአካልና የስነ ልቦና ጥቃት “ለስልጣናችን አስጊ የሆነውን ሁሉ ገና ከእንጭጩ መቅጨት አለብን” ከሚል ትውልድ ገዳይ ፓለሲ የመነጨ መሆኑን የአደባባይ ሚስጢር እየሆነ መጥቷል።

- በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ በተለይም በህወሓት ሞኖፓላዊ አገዛዝ የሚተዳደረው በትግራይ ህዝብ ላይ እየደረሰ ስላለው ግፍና መከራ ሌላውን ለናንተ ልተውና “እውነት ህወሓት የትግራይ ህዝብ ነፃ አውጪ? ለሚለው ጥያቄ ሚዛናዊ ፍርድ ይኖራችሁ ዘንድ የዓረና አባል የነበሩ በአቶ አረጋዊ ገብረዮሐንስ ላይ የደረሰ አሰቃቂ የሞት አደጋ ማየቱ በቂ ነው የሚል እምነት ስላለኝ በአጭሩ ጠቅሼ

ወደ ሌላው ነጥብ ልለፍ። ቀደም ሲል በተለያዩ ድህረ ገፆች እንደ ተጠቀሰው ሁሉ አቶ አረጋዊ ገብረዮሐንስ ዓረናን በመወከል በአራተኛው ሀገራዊ ምርጫ ለፌዴራል ፓርላማ ዕጩ ተወዳዳሪ ሆኖ የቀረበ ነበር። አቶ አረጋዊ በድርጅቱም ሆነ በተንቀሳቀሰበት ቦታ ሁሉ የህዝብ ተቀባይነት፣ ጥሩ

- የመግባባትና የማሳመን ችሎታ የነበረው ወጣት ምሁር ነበር። አቶ አረጋዊ ለህልፈት ከመዳረጉ ከጥቂት ቀናት በፊት አቶ መለስ ዜናዊ 37ኛው የህወሓት ልደት በዓል ምክንያት በማድረግ በመቀሌ አደባባይ በመገኘት ዓረና ትግራይን እንደጠላት በመፈረጅ በጠላቱ ላይ እንዲነሳ ለትግራይ ህዝብ የክተት ጥሪ አቅርበው እንደነበር ይታወሳል።

የክተት አዋጁ ሁኔታ አደገኛ ቢሆንም ቅሉ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ጥሪ በትግራይ ህዝብ ዘንድ ተቀባይነት አላገኘም። ሆኖም እነ አቶ መለስ ዜናዊ ህዝቡ "እኔን አይተህ ተቀጣ" የሚልበትና አደናግጠው በአቋራጭ ምርጫውን የሚያሸንፉበት ሌላ ዘዴ መፈለግ ግድ ሆነባቸው። በዚህ ምክንያት ዓይናቸው በአቶ አረጋዊ ገ/ዮሐንስ ላይ አረፈ። አቶ አረጋዊ ከመገደሉ በፊት የድህንነት አባላት በሄደበት ሁሉ ይከታተሉት እንደነበር በወቅቱ በራሱ አንደበት ይናገር ነበር። ሁኔታውን በመረዳት መስዋእትነት ለመክፈል ዝግጁ እንደሆነ በመግለፅ ህዝቡንና አላማውን ተማምኖ እንቅስቃሴውን ቀጠለ። አቶ አረጋዊ በእጁ የያዘው ወረቀትና ብዕር ብቻ ነበር። ሌላ ትጥቅ አልነበረውም። ለህዝቡ የሚያስተምረውም ስለጥላቻና ቂም በቀል ሳይሆን ስለ አንድነት፣ ሃቀኛ ዲሞክራሲ፣ ፍትሕ፣ የሕግ የበላይነትና መልካም አስተዳደር መከበር ነበር። ነገር ግን እንደገመተው ብዙ አልቆየም። ከጥቂት ቀናት በኋላ አቶ አረጋዊ ሌሊት ከተኛበት ክፍል ተቀስቅሶ በሚዘገንንና በሚያስደነግጥ መልኩ በቤቱ ውስጥ በወለል ላይ እንደበግ አጋድመው አረዱት።

ነብሰ ገዳይ ቅጥረኞቹም የትም አልሸሹም። እንዲያውም ተዝናንተው ማንም ሳይጠይቃቸው ራሳቸው እጃቸውን ለፖሊስ ሰጡ ተባለ። ስለሁኔታው በገለልተኛ አካል እንዲጣራ ከየአቅጣጫው ጥሪ ቢቀርብም ገና የሃዘን ድንኳኑ ሳይፈርስና ሃዘንተኛውን ሳይረጋጋ የፍርዱ ሂደት ሳምንት ባልሞላ ውስጥ ተጠቃልሎ ፋይሉ ተዘግቷል ተባለ። ከዚያም ዳኛ በሰጠው ፍርድ ላይ ጣልቃ መግባት አይቻልም በሚል የማጣራቱን ጥያቄ ተቀባይነት ሳያገኝ ቀረ። በፍርዱ ቀንም የቅርብ ጓደኞቹ ፍርድ ቤት ገብተው ጉዳዩን እንዳይከታተሉ ተከልክሏል። ከነብሰ ገዳይ ቡድኑ አንዱ ለ15 ዓመታት ተፈርዶበታል ቢባልም ከዚያ በኋላ በእስር ቤት ይኖር አይኖር የሚታወቅ ነገር የለም። ሌሎች ግብረ አበሮቹ ደግሞ በነፃ ተለቀው በሰላም ይኖራሉ። ከዚህ ሁሉ የሚገርመውና የሚያሳዝነው የአቶ አረጋዊ ገ/ዮሐንስ ሞትና የፍርድ ሂደቱ ድራማ ብቻ አይደለም። ሰውዮው ከሞተ በኋላ በቤተሰቡ ላይ የደረሰው መበታተን፣ መፈራረስና መንከራተት ነው። ስድስት ልጆቹና የሚቹ ወንድም ወደ ሱዳን ተሰደዱ። ሚሲቱ በድንጋጤ አቶ አረጋዊ ከሞተ ከአንድ ወር በኋላ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይታለች። እንግዲህ እግዚሄር ያሳያችሁ! ለትግራይ ህዝብ ነፃነት፣ ልማትና ዲሞክራሲ ማለት ይኸው ነው።

## ሙሱና በሀገራችን ከኤድስ በላይ ወረርሽኝ በሽታ ሆነዋል

መሱና በኢትዮጵያ ከኤድስ በላይ ወረሰርሽኝ በሽታ ሆኗል" የሚለው አገላለፅ በአካባቢው በሕብረተሰቡ ዘንድ ከሚነገሩት የብሶት መግለጫዎች የወሰድኩት አባባል ነው። ይህ ብቻ አይደለም በየቀኑ ህዝቡ አድጓል እያሉ በመንግስት መገናኛ አውታሮች የህዝቡን ጆሮ የሚያደነቁሩትን የመንግስት ጋዜጠኞች በማህል ሀገር "ለማ" የሚል ስያሜ ተሰጥቷቸዋል። በትግራይ አካባቢ ደግሞ ለማ የሚለውን ቃል በትግርኛ ተርጉመው "ላማ" በሚል ስያሜ ይጠቅሱታል። ላማ ማለት በትግርኛ ምላጭ ማለት ነው። ምላጭ ማለት ደግሞ ከሙሱና ጋር ተያይዞ የሀገር ሃብት የሚነጭ ማለት ነው። በሌላ መልኩ ደግሞ የትላንት ታሪክ ቆርጦ በመጣል ያለነበረውና ያልተደረገውን የሚያሳይ ማለት ነው፡፡ በአንድ አጋጣሚ ከሰዎች ጋር ቁጭ ብለን ስለችግሩ ስናወራ ህዝቡ የስርዓቱን አስከፊነት በሙሱና አማካይነት ሲገልፅ እንዲህ በማለት ነግረውኛል። "አንድ የጤና ካድሬ ህዝቡን ሰብስቦ ስለኤድስ በሽታ አስከፊነት

ሲያስተምር ወደ ዝርዝር አርእስቱ ከመግባቱ በፊት ተሰብሳቢዎቹን "አመንምኖ ገዳይ ምንድን ነው?" ብሎ ይጠይቃል። ህዝቡ በተለይም ወጣቶቹ ዝም አሉ። ካድሬው "ተናገሩ እንጂ" እያለ ደጋግሞ ይጎተጉታቸዋል። አንድ አዛውንት ብድግ ብለው እንደ ቀልድ አስመስለው እየሳቁ "ስማ ልጄ ሀገርንና ህዝብን አመንምኖ እየገደለ ያለው "ሙሱና (ግዕዚይና) ነው" ብለው ሲመለሱ ቤቱ በሳቅም በጭብጨባም ቀለጠ አሉ። እውነት ነው! በሕብተሰቡ ዘንድ በየአካባቢው የሚነገሩ የብሶት መገለጫዎች ብዙ ናቸው። አልፎ አልፎም በቪድዮ ካሜራም ሆነ በማስታወሻ ለታሪክ ያስቀመጥኩዋቸው አሉኝ። ምናልባት ለወደፊት ጊዜና ሁኔታ ሲፈቅድ ለማቅረብ እሞክራለሁ።

አዎ!! ሙሱና በአሁኑ ግዜ በዓለም ላይ ብዙ ሀገሮችን ለድህነት የዳረገ፣ የሀገርና የህዝብ ሀብት ያባከነ፣ የዕድገትና የዲሞክራሲ ባላንጣ የሆነ በዓለም ማሕበረሰብ ዘንድ የተወገዘ እርኩስ ተግባር ነው። ከራሳችንና ከሌሎች ሀገሮች ልምድ እንደምናየው አብዛኞቹ ዓይን ላወጣ ሙሱና የተጋለጡ ሀገሮች ነፃ ህዝባዊ ኢንስቲቱሽን፣ ነፃ የፍትሕና የዲሞክራሲ ተቋማት፣ ግልፅነትና ተጠያቂነት ያለው መልካም አስተዳደር የሌላቸው፣ በጥቂት ፈላጭ ቆራጭ አምባ ገነን መሪዎች ብቻ የሚተዳደሩ ናቸው። መሪዎቹም ውለው አድረው ከሀገር መኮብለላቸው የማይቀር መሆኑን ስለሚያውቁ የሀገር ችግር ከማስቀደም ይልቅ ለራሳቸው ለክፉን ብለው ገንዘብና የከበረ ንዋይ ወደ ውጭ ያሸሻሉ። ለትውልድ የሚሆን ስራ ከመስራትና ከማሰብ ይልቅ ለራሳቸው ቤተሰብና ለልጅ ልጆቻቸው ስለሚያወርሱት ሀብት ለማካበት ይጨነቃሉ። ከራሳቸው ህዝብ ይልቅ የውጭ ባለሀብቶችን ይተማመናሉ። ስልጣናቸውን ለማቆየትና ለማጠናከር ሲሉም እጃቸውን በንፁኃን ደም ስለሚነከር የመጨረሻ ቀናቸው ሲደርስ ሀገር ውስጥ የመኖር ተስፋቸው ስለሚመነምን ወደ ውጭ ሀገር የሚያመልጡበት ሁኔታ ያመቻቻሉ። ገንዘብ ከሰው በላይ ይናገራል ነውና ሀገርንና ህዝብን ካደቀቁ በኋላ እንደምን ብለው ከሀገር ያመልጣሉ።

በኢትዮጵያ የነበረውና አሁን ያለው ሁኔታ ሲታይም ከዚህ የባሰ እንጂ ያነሰ አይደለም። ደርግ የቀዳማዊ ሀይለ ስላሴ ስርዓት ሲያወግዝ ንጉሱ ለልጆቻቸው የሚበቃ አስራ አንድ ቢሊዮን ዶላር ወደ ስዊዘርላንድ ባንክ አሸሽቷል እያለ ከወሎ ረሃብ እልቂት ጋር እያነፃፀረ ለህዝብ ሲያሳይ ነበር። ለምሳሌ የወሎ ህዝብ ተርቦ ጥላሁን ገሰሰ "ዋይ ዋይ ሲሉ" እያለ ሲዘፍን አንድ የንጉሳን ቤተሰብ ለሰርጉ ዕለት በአንድ መቶ ሽሕ ዶላር በጣሊያን ሀገር በትእዛዝ የተሰራውን ኬክ ሲቆረስ በተለቭዥን ይታይ ነበር። በወቅቱ ይህንን ሁኔታ ያየና የሰማ ህዝብም በመገረም ለጉድ አለ። ደርግም ስልጣኑን ካመቻቸ በኋላ በተራው ብዙ አልቆየም የአየር በአየር ዝርፊያና የተደራጀ ሌለብነት ተጧጧፈ። ሀገሪትዋም በአንድ በኩል ሁሉም ወደ ጦር ግንባር በሚል መፈክር በሌላ በኩል ደግሞ የኢሰፓ ካድሬና የባለስልጣናት ዓይን ያወጣ ሙሱና ምክንያት ኢኮኒሚዋን ደቀቀ። ዓመታዊ ዕድገትዋም ከዜሮ በታች ወረደ። በመሪዎችና በህዝቡ መካከል የንሮ ልዩነቱ የሰማይና የምድር ያህል ሆነ። በሙሱናና በአፈና የተገነባ የደርግ ስርዓትም እየተፈረካከሰና እየተሰነጣጠቀ መምጣቱ የተረዱት መሪዎችም ለክፉ ቀን የሚሆን መውደቂያቸውን ማመቻቸትና ሃብት ማሸሽ ጀመሩ። በመጨረሻም ራሳቸውን እንደ አፄ ቴድሮስ ሲያመሳስሉ የነበሩት ኰሎኔል መንግስቱ ሀይለማሪያምም ሽልክ ብለው ከሀገር ወጡ።ይህንን ሁኔታ ሲከታተል የነበረ ህዝብም "መቆየት ደጉ ብዙ አሳየን" ተባለ።

ህወሓት/ኢሕአዴግም የነፃነት መዝሙር እየዘመረ፣ የዲሞክራሲ ካባ ለብሶ በትረ ስልጣኑን ጨበጠ። ልክ ደርግ የሃፄ ኃይለስላሴን ስርዓት ለማጥላላት የተጠቀመበትን ዘዴ ሁሉ ህወሓት/ኢሕአዴግም በተራው የደርግን ስርዓት አረሜኔነትና ዘራፊነት በተመሳሳይ ዘዴ ለህዝቡ ማሳየት ጀመረ። የኢትዮጵያ ሃብት በደርግ ባለስልጣናት ስለተዘረፈ ባዶ ካዝና ነው የተረከብነው ተባለ። ለምሳሌ ኢሕአዴግ አዲስ አበባ እንደገባ በመጀመሪያዎች አካባቢ አቶ መለስ ስለ የደርግ ስርዓት ሙሱና ሲናገሩ "የደርግ ባለስልጣናትና ሰራዊቱ ቢፈተሹ በቤታቸው ውስጥ የሚገኙት ዕቃዎችና ንብረቶች ገና ሒሳባቸውን ያላወራረዱ ናቸው"

ብለው እንደነበር አስታውሳለሁ። ታዲያ!! የአቶ መለስ ዜናዊ አገዛዝ - ህወሓት/ኢ.ህአዴግ ካለፉት ስርዓታት በተለይም ከደርግ ምን ተማረ? ህዝቡስ ምን ተመኩሮ ወሰደ?

የአቶ መለስ ዜናዊ አገዛዝ ካለፉት ስርዓታት የወረሰው ትልቁ ነገር አፈናና ሙስና ነው። ከላይ በሰፊው እንደተጠቀሰው የአፈናና የሙስና ተግባራት ደግሞ የአንድ ፀረ ዲሞክራሲ ስርዓት ባህርይ መገለጫዎች ናቸው። አገዛዙም ወደ ሙስና የገባው አሁን ሳይሆን ልክ ህወሓት/ኢ.ሕአዴግ አዲስ አበባን እንደተቆጣጠረ ማግስት ነው። በተለይም የድርጅቱን የድህንነት አባላትና ከፍተኛ ካድሬዎች ዋና ዋና የኢኮኖሚ አውታሮችን እንዲቆጣጠሩና እንዲያረጋጉ በተመደቡበት ወቅት የህዝብና የመንግስት ሀብት ለመዝረፍ ትልቅ ዕድል አግኝቷል። ለምሳሌ በባንክ አካባቢ የነበረው የመንግስትና የንጉሳን ቤተሰብ ወርቅና ሌሎች የከበሩ ንዋያት ተዘርፏል የሚል ስሞታ ተደጋጋሚ ይቅርብ ነበር። በዚሁ ጉዳይ በመካከላቸው ትልቅ ሓሜት፣ ግጭትና መካሰስ ተፈጥሮ አንዳንዶቹ እጅ ከፍጅ ተይዘው ሲታሰሩ የተወሰኑ ደግሞ የያዙት ይዘው ከሀገር የኰበለሉም እንዳሉ ይታወቃል።

ሙስና በሰርዓቱ ውስጥ ስር እየሰደደ መጥቶ ከተራ አባል እስከ ከፍተኛ ባለስልጣናት ድረስ ሰንሰለት ያለው ዝርፊያ ተጀመረ። በሽግግር ጊዜ ጠቅላይ ሚኒስትር በኋላም ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር የነበሩት አቶ ታምራት ላይኔም የሙስና ዋና ተዋናይ ሆነው ተገኙ። አቶ ታምራት ላይኔ ቢታሰሩም በልጃቸው ስም ወደ ውጭ አሸሹት የተባለውን በሚሊዮን የሚቆጠር የቡናና የከበረ ሃብት ሽያጭ ገንዘብ አልተመለሰም። ከሳቸው በኋላም ሙሱናው እየባሰ ሄደ እንጂ አልቆመም። እንደ ወረርሽኝ በሽታ እየተዛመተ የሁሉም ባለስልጣናትና ካድሬዎቻቸው ደም ስር እየሆነ መጣ። ከጊዜ ወደ ጊዜ እተባባሰ መጥቶ አሁን ሊቆጣጠሩት ወደ ማይችሉበት ደረጃ ደርሷል። የዝርፊያው ስፋትም ከግለ ሰቦች ሌለብነት አልፎ ተቋማዊ መልክ ይዟል። በተደራጀ መልኩ የህዝብና የሀገሪትዋ ሃብት ወደ ውጭ ማሸሽ፣ ለግልም ሆነ ለቡድናዊ ጥቅም መሯሯጥ፣ ከውጭ ኢንቨስቶሮች ጋር ተመሳትትሮ አብሮ መዝረፍ፣ ስልጣንን መከታ በማድረግ ፍትሕ ማጣመም፣ ወዘተ የመሳሳሉ ዓይኑ ያወጡ ዝርፊያዎች በሰፊው ቀጥሏል። በመሆኑም የአቶ መለስ ዜናዊ አስተዳደር ሙስና ለሁለት ነገሮች ይጠቀምበታል። በአንድ በኩል የሀገሪትዋን እንጡራ ሃብት መዝረፊያ መሳሪያ አደርጎ መጠቀም ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ሙስና የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ስርዓት ማጠናከሪያ ማድረግ ነው። ይህ ማለት በገንዘብም ሆነ በስልጣን እየደለሉ አባላትንና ደጋፊን ማፍራት፣ በሙስና የተዘፈቁ ሰዎች ደግሞ እያስፈራሩ የድርጅቱን ወይም የስርዓቱን አገልጋይ እንዲሆኑ ወይም በማስፈራራት ፀጥ ረጭ ብለው እንዲገዙለት ማድረግ የመሳሰሉ ናቸው።

## ማጠቃለያ

እስካሁን የጠቀስናቸው እውነታዎች አጠቃልለን ስናየው የህወሓት/ኢ.ሕአዴግ ስርዓት ከራሱ ውስጠ ፓርቲ ግንኙነት ጀምሮ ከሀገርና ከህዝብ ጋር መሰረታዊ የጥቅም ቅራኔ ያለበት ፀረ ደሞክራሲ ስርዓት ነው። እንደ ድርጅትም ሆነ እንደ ግለ መሪዎች በሀገር ጉዳይና በህዝብ ጥቅም ላይ ምን እየሰሩ እንደሆነ ጠንቅቀው ያውቃሉ። ሌላ ቀርቶ ራሳቸው ያፀደቁትን ሕግና ደንብ እንኳን በአግባቡ እንዲከበር አይፈልጉም። የማይፈልጉበት ምክንያት ደግሞ የሕግ የበላይነት ከተከበረ ተመልሶ እነሱን የሚጠይቃቸው መሆኑን ስለሚያውቁት ነው። ይህ ዓይነቱ ተግባር ደግሞ የትም ይብቀል የትም በሁሉም ጨቋኝና አምባ ገነናዊ ስርዓት የሚታይ ባህርይ ነው። ስለዚህ ሙሰና የአቶ መለስ ዜናዊ አገዛዝ ደመ ነብስ በሆነበት ዘመን ለህዝብ የሚጠቅም ዘላቂ ልማት ይመጣል ብሎ ማመን ልክ ከእባብ እንቁላል እርግብ ይወለዳል ብሎ እንደ መጠበቅ ያህል ነው።

አንዳንድ ሰዎች ሙስና የማያቋርጥ የሰው ልጅ ባህርይ አድርገው ይወስዱታል። እኔ ግን በዚህ አልስማማም። ዋናው በቅድሚያ መታየት ያለበት የሙስና ምንጭ ምንድን ነው? የሚለው ነው። ከላይ

እንደተጠቀሰው የሙሱና ምንጭ ብልሹ አስተዳደር ነው። በአንድ ሀገር ነፃ ህዝባዊ፣ የዲሞክራሲና የፍትሕ ተቋማት ካሉ፣ የሕግ የበላይነት ከሰፈነ፣ ተጠያቂነትና ግልፅነት ያለው መልካም አስተዳደር ከተረጋገጠ ግለ መሪዎችም ሆኑ የተወሰኑ ቡድኖች በሀገርና በህዝብ ጥቅም ላይ እንደፈለጉ መቀለድና መዝረፍ ወይም ከሕግ በላይ ለመሆን አይችሉም። የአሜሪካ ፕሪዚዳን ባራክ ኦባማ በአንድ ወቅት ስለአፍሪቃ ሲናገሩ "አፍሪቃ ሀገሮች ከድህነት መላቀቅ የሚችሉት ኀበዝ ወይም ብልጥ መሪዎችን በማፍራት ሳይሆን ብልጥ ወይም ጠንካራ ተቋማትን (ኢንስቲቱሽን) በመገንባት ነው "ብለው እንደነበር ይታወሳል። ለእኛም ለሀገራችን ብቸኛው መፍትሄ ራሳቸውን ከሀገር፣ ከህዝብና ከሕግ በላይ የሆኑትን አምባ ገነን መሪዎችን ከማመለክና ከመመገብ ይልቅ ዓለም የደረሰበትን የአስተሳሰብ ደረጃ ለመድረስ ሁላችንም በእኩልነት የሚያገለግሉ ነፃ ተቋማትን መፍጠር፣ መገንባት፣ መንከባከብና ማጠናከር የዕድገታችንና የአንድነታችን ዋስትና ነው የሚል እምነት አለኝ።

በተረፈ በሀገራችን ወቅታዊ ጉዳይ ላይ ያጠናቀርኩትን ሌሎች ተመሳሳይ ዘገባዎችን በማከል በክፍል ሶስት ፅሑፌ ይገፔ እቀርባለሁ። እስከዚያ ለሳምንት ሰው ይበለን ደህና ሰንብቱ።

ኢትዮጵያ ሀገራችን ለዘላለም ትኑር

ኢሜይል sgbtsait@gmail.com